# የሰቆቃውን ዘመን ለማሳጠር. . .

ዮናስ 11-08-17

ኢህአዴግ በ1983 ዓ.ም አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ የአገራችን የሰላምና ደህንነት ሁኔታ በወሳኝ መልኩ መሻሻል ያሳየበት ቢሆንም ሃገራችን በርካታ ፈተናዎች ተደቅነውባት የነበረ መሆኑ ይታወሳል። ለሰላምና መረጋገት እንቅፋት የነበረው በዋናነት የደርግ አፈና መዋቅር በህብረተሰቡ ውስጥ የተበተነ በመሆኑ በአብዛኛው የአገራችን አካባቢዎች ሠላምና መረጋጋት እንዳይኖር ማድረጉ ሲሆን፤ በተለይም ከአፈና መዋቅሩ ጋር አብሮ የተበተነው በርካታ የጦር መሣሪያ ዝውውርና ዘረፋ፣ ያልተረጋጋ ኢኮኖሚና ከእጅ ወደ አፍ የሆነው የህዝቡ ኑሮ ለሃገራዊው ሰላምና መረጋጋት እጅግ ፈታኝ እንዲሆን አድርጎ የነበረ መሆኑ መሰረታዊው ጉዳይ ነው።

በሌላ በኩል የሽግግሩ መንግስት የሚመራበት በአገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ያሉ የተለያየ አመለካከትና አስተሳሰብ ያላቸው ወገኖች በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል ያሉ ሁሉ ሃሳቡንና አማራጭ አመለካከቱን በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲሰበሰብ የሚያደርግ ቻርተር የተረቀቀበት፣ ውይይት የተደረገበት፣ የፀደቀበትና በዚሁ የተመራበት ስለነበር ዓይነትኛ የሰላም ዋስትና የሚያረጋግጥ አገራዊ ሁኔታ ፈጥሮ የነበረ መሆኑም ይታወሳል።

በዚህ የሽግግር መንግስት ወቅት በቻርተሩ መሰረት የሃገራችንን ሰላምና መረጋጋት እንዲያስጠብቅ ሃላፊነቱን የወሰደው የኢህአዴግ ሰራዊት ሲሆን የኦነግ ሰራዊትም የህዝቡን ሃላፊነት እንዲረከብና የበኩሉን ሚና እንዲወጣ የሚያደርግ ሁኔታ ተመቻችቶ ነበር። ይህ ሁኔታ ብዙም ሳይቆይ የኢህአዲግ ሰራዊት በቻርተሩ የተቀመጠውን የሽግግር መንግስት ተልዕኮ በብቃት እየተወጣ የህዝቡን ሰላምና ደህንነት በአግባቡ በመጠበቅ ሲቀጥል የኦነግ ሰራዊት ግን ቻርተሩን በመጣስና የኢትዮጵያን ህዝብ በመክዳት እጅግ ጭካኔ የተሞላበትና የሚዘገንን ግድያና ጭፍጨፋ በሰፈረባቸው ሀረር፣ ባሌና በሌሎችም የአገራችን አካባቢዎች በማካሄዱ የሽግግር ዘመኑን ሰላምና ደህንነት ፈታኝ አድርጎት የነበረ መሆኑም የሚታወስ ነው። አገር በቀልና ዓለም አቀፍ የሽብር ቡድኖችም አንዳንድ አደጋ በማድረስ የህዝቡን በሰላም የመኖር ዋስትና አደጋ ላይ እንዲወድቅ ከፍተኛ ሙከራ ያደረጉበት ወቅት ነበር ማለት ይቻላል። እነዚህን ፈተናዎች ለማለፍና ዓይነተኛ ሰላምና መረጋጋት እንዲመጣ ለማድረግ የሽግግር መንግስቱ በዋናነት የሰላም ምንጭም ባለቤትም ህዝቡ እንዲሆን የሚያደርግ የማይነቃነቅ አቋም ይዞ ህብረተሰቡ በየአካባቢው የራሱን ሰላም የሚጠብቅበት ሁኔታና አደረጃጀት መፍጠር በመቻሉ አይነተኛ ሰላም እንዲመጣና መረጋጋት እንዲፈጠር ማድረግ ችሏል።

በሽግግር መንግስቱ ይመራ የነበረውና ዛሬ የኢፌደሪ የመከላከያ ሰራዊት በመባል የሚታወቀው የወቅቱ የኢህአዴግ የመከላከያ ሰራዊት በአንድ በኩል በአገር ውስጥ በተለያየ ቦታ የተፈለፈሉ ፀረ ሰላም ሃይሎችን በመምታትና የህዝቡን ሰላም የማረጋገጥ ሃላፊነቱን በብቃት እንዲወጣ የሚያደርግ ሥራ ከመስራቱም በላይ ህዝባዊ ባህርይ ያለው ሃይል መሆኑንም በየግዳጆቹ አፈፃፀም ሂደት የሚያስመሰክሩ ሥራዎችን ሰርቷል። ሌሎች የፀጥታ መዋቅሮችም መሰረታዊ የህዝቡን ሰላምና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ የተለያዩ የሽብርና የአመፅ እንቅስቃሴዎችን በመሳሪያና በተደራጀ መንገድ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ተመጣጣኝና ህጋዊ እርምጃ በመውሰድና የህዝቡን የሰላም ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ሥራ ከህዝቡ ጋር ሰርቷል። በጥቅሉ የሽግግር ዘመኑ እጅግ ለሰላምና ደህንነት ጠንቅ የሆኑ ከላይ የተመለከቱ ነባራዊ ሁኔታዎች የነበሩ ቢሆንም ሁሉንም በስኬትና በአሸናፊነት በመወጣት የሃገራችን ህዝቦች ዋስትናና ቃል ኪዳን ሰነድ ለሆነው ህገ-መንግስት መፅደቅ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።

በዚሁ ድል የተገኘው የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የሃገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ለመጀመሪያ ጊዜ በፖለቲካ መድረክ እኩል የመደመጥና የመሳተፍ መብት እንዲያገኙ ያስቻለ ከመሆኑም በላይ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍልና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ዋስትና የሰጠ ነው። ህገ መንግስቱ ለዘመናት ያልተመሰሉ የዜጎቻችን የማንነት፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የሃይማኖትና ራስን በራስ የማስተዳደር በአገሩ የመጠቀምና የማደግ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ያስቻለ ከመሆኑም በላይ አንድ የጋራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ ለመገንባትም የጋራ ቃል ኪዳናቸውን ያስቀመጡበት ሰነድ በመሆኑ መሰረታዊ የሰላም ዋስትናችን ነው ብሎ ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል። ህገ መንግስቱ አዲሲቷን ኢትዮጵያ የፈጠረና እየገነባ የሚገኝ ሰነድ ነው የሚባልበት ምክንያትም ይኸው ነው።

ህገ መንግስቱ ዓለም አቀፍ ህጎችንና ድንጋጌዎችን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ ያስቀመጠና የተቀበለ ከመሆኑም በላይ ከሰው ልጅች ተፈጥሮዋዊ ድንጋጌዎች የሚመነጩ መብቶችን ሙሉ በሙሉ ያካተተ፤ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ያስከበረ፤ ዜጎች በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በዕድሜ፣ በፖለቲካ አመለካከትና አስተሳሰብ አድልዎና ልዩነት ሳይኖራቸው በህግ ፊት እኩል የሚሆኑባቸው ድንጋጌዎችንም ያካተተና፣ በተግባርም የቀየረ በመሆኑ የአገራችን ህዝቦች የሰላምና ደህንነት ጥያቄዎች በመሠረታዊ መልኩ እንዲፈታ አስችሏል።

ህገ መንግስቱ ባጐናፀፈን ድልና ስኬት የሃገራችን የመንግስት አደረጃጀቱም ፌዴራላዊ የመንግስት ቅርፅ እንዲይዝ ተደርጓል። በዚህም የሃገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ማንነታቸውንና አሰፋፈራቸውን ማእከል ያደረገ አስተዳደራዊ አደረጃጀት ተፈጥሮላቸው አካባቢያቸውን የሚያስተዳድሩበትና የሚያለሙበት፤ ከልማቱም ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት የተፈጠረ ከመሆኑም በላይ በፌዴራልና በየደረጃው ባሉ የፖለቲካ መድረኮችና የህዝብ ምክር ቤቶች በመርህ ላይ የተመሠረተ ውክልና እንዲኖራቸው በማደረጉና ይህም በተግባር ውጤት ያመጣ በመሆኑ የሃገራችን ህዝቦች የሰላምና ደህንነት ጥያቄያቸው እንዲፈታ ተደርጓል፡፡

ለዚህ ሁሉ ስኬት የጀርባ አጥንት የነበረው፤ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የነበረው ሰራዊት የሽግግር ዘመኑን ተልዕኮና ግዳጅ በብቃት ከተወጣ በኋላ ህገ መንግስቱ ሲፀድቅ የኢፌዲሪ መከላከያ ሃይላችን አደረጃጀትም ሣይንሳዊና የሃገራችንን ብሄር ብሄረሰብ መምሰል እንዳለበት ውሳኔ በማግኘቱ በክፍለ አህጉሩም ሆነ በአለም አቀፍ አደባባይ የሚያኮራ በጀግንነቱና በህዝባዊነቱ የአገራችን አለኝታ የሆነ የአገር መከላከያ ሃይል ሊገነባ ችሏል። በዚህ ግንባታ ሂደት በትጥቅ ትግሉ ወቅት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ታጋዮች ጭምር ሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ተሳትፎ እንዲኖር በመወሰኑ ምክንያት እነሱም አምኖ የተቀበሉበትና ሂደቱም በነፃ ውይይትና ዲሞክራሲያዊ አካሄድን የተከተለ እንዲሆን ተደርጎ የተገነባ ሰራዊት ነው። ይህ አደረጃጀትም ለመከላከያ ሃይላችን የስኬት ጉዞ ዓይነተኛ ምክንያት ሲሆን በተከታታይ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የተሰጡ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎችም ከውስጥም ሆነ ከውጭ በህገ መንግስታዊ ሥርዓቱና በህዝቡ ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ በበቂ አቅም የሚመክት ሃይል እንዲሆን አድርጐታል።

ለዚህ አንዱ ማሣያ በ1990 ዓ.ም በሻዓቢያ ፀብ አጫሪነት የተፈፀመውን ወረራ የአገራችን መንግስትና ህዝቡ ባልገመተውና ባላሰበው መልኩ የተፈፀመብን ቢሆንም ይኸው የህገ-መንግስታዊ ሥርዓታችን ውጤት የሆነ መከላከያ ሃይላችን የጀግንነት ገድል በመፈፀም የተቃጣብንን የእብሪት ወረራና ጦርነት በድል እንድንወጣ በማስቻሉ የሰላማችን አለኝታ ሆኖ መቀጠል አስችሎታል። በዚህ ሳያበቃ እንደ አሊ-ኢትሃድና አብነግ የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ አሸባሪ ቡድኖች ከአገር አቀፍ አሸባሪ ቡድኖችና አካላት ጋር በተናጠልና አንዳንዴ በጋራ የሚመስለው የሽብር አደጋ በተደጋጋሚ ለመፈፀም የሞከሩ ቢሆንም በወሳኝ መልኩ ጀግናው መከላከያ ሃይላችንና ሌሎች የፀጥታ መዋቅሮች በጋራና በቅንጅት ህብረተሰቡን በማሳተፍ በሰሩት ጠንካራ ሥራ የሃገራችን ህዝቦች የሰላምና ደህንነት ሁኔታ አስተማማኝ እንዲሆን አድርጓል።

ጀግናው መከላከያ ሃይላችን የአገራችንን ሰላም ከማረጋገጥ በተጨማሪ በአፍሪካ ህብረትና በተባበሩት መንግስታት የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች በመሳተፍ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበ ከመሆኑም በላይ የአገራችንንና የህዝባችን ገፅታ በበጎ እንዲገነባ በማድረግ ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል።

ኢትዮጵያ የምትገኝበት የክፍለ-አህጉሩ ክፍል የአፍሪካ ቀንድ በመሆኑና ይህ አካባቢ ደግሞ በተለያየ ምክንያት የሰላምና መረጋጋት እጦት እየተጋረጠበት የሚገኝ አካባቢ ሲሆን ይህንን ጀግናው መከላከያ ሃይላችን ኃላፊነቱን ተረክቦ ግዳጁን በብቃት ተወጥቷል፤ እየተወጣም ይገኛል። በተለይም በሶማሊያ በተፈጠረው ጠንካራ መንግስት አለመኖሩን ተከትሎ የሽብርተኛ ድረጅቶችን እንቅስቃሴ ለመምታትና ለማክሸፍ የኢፌዲሪ መከላከያ ኃይል የከፈለው መስዋዕትነትና ያረጋገጠው ሰላም በሰላም ወዳድ ህዝቦች ዘንድ እየተወሳ የሚኖር የጀግንነት ተግባር ለመሆን በቅቷል። ከዚህ በተጨማሪ በአንዳንድ የአፍሪካ አገራት የተፈጠረውን ግጭት ተከትሎ ጀግናው መከላከያ ሃይላችን፣ በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲ፣  በላይቤሪያ፣ በደቡብ ሱዳን፣ በሰሜን ሱዳንና በሌሎች የተባበሩት መንግስታት ፀጥታው ም/ቤትንና የአፍሪካ ህብረት ውሳኔን ተከትሎ በመግባት የተሰጠውን ግዳጅ እጅግ በሚያኮራ ውጤት በመፈፀም በአንድ በኩል ጀግንነቱንና ህዝባዊነቱን ሲያስመሰክር በሌላ በኩል ዋነኛ የውጭ ዲፕሎማሲያችን ሞተር በመሆኑ የአገራችንን ገፅታ በበጎ በመገንባት ከፍተኛ ድርሻ ተወጥቷል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሃገራችን ባለፉት ዓመታት ለሰላማችን እጅግ ጠንቅ የሆኑ እንቅስቃሴዎች እየታዩ እና በስፋትም ሆነ በጥልቀት እየጨመሩ ነው። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ደግሞ አሸባሪ በሆኑ ድርጅቶች ኦነግ፣ ግንቦት 7፣ አርበኞች ግንባር፣ አብነግ እና ሌሎች ተመሳሳይ የሆኑና በሻዓቢያ መንግስት የሚመሩ ተላላኪዎች ሲሆኑ በሃገር ውስጥ ኮንትሮባንዲስቶች እየታገዙ፤ ዋንኛ ተልዕኮዋቸውም የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች የተቀዳጁትን ህገ መንግስታዊ ሥርዓት በማፍረስ የኪራይ ሰብሳቢነት ከርሳቸውን መሙላት ነው። ይህንን የተረዳው መንግስታችን የሽብርና የጠላት ተልዕኮን ለመከላከል የሚያስችል ፖለቲካዊና ህጋዊ ሥርዓቶች በመዘርጋት ትክክለኛ የትግል አቅጣጫ አስቀምጧል። እነዚህ እንቅስቃሴዎች መፈታት ከተገባቸውም በዚሁ አቅጣጫ ብቻ እንጂ ከላይ የተመለከቱ ተልእኮዎችን በብቃት በመወጣት ለገጽታ ግንባታ በተረፈው የሃገር መከላከያ ሰራዊት ሊሆን አይገባም። በተለይም በአገራችን ተግባራዊ በሆነው ፀረ ሽብር አዋጅ የእነዚህን አሸባሪ ድርጅቶችንና ኮንትሮባንዲስቶች ቅስም መስበር ይቻላል።

እነዚህ ፀረ ሰላም ድርጀቶችና ኮንትሮባንዲስቶች የህዝባችንን ህይወት የቀጠፉ እና በርካቶችን እንዲፈናቀሉ ካስቻለ ተግባራቸው አሁንም ሊቆጠቡ የፈለጉ አይመስሉምና አቅጣጫውን በመከተል ብቻ ከወዲሁ እርምጃ መውሰድ እንጂ ሃገራዊና አህጉራዊ ተልእኮ ያለውን ሰራዊት በዚህ ስራ መጥመድ አይገባም። በኮንትሮባንዲስቶቹ ህገ ወጥ ሴራ  በሺዎች የሚቆጠሩ ንፁሃን ዜጎች የጥቃቱ ሰለባ ሆነዋል፤ ቀላል የማይባል ንብረትም ወድሟል። ሆኖም ግን  እነዚህን ሃይሎች በተዘረጋው ጠንካራ የፀጥታ መዋቅር ማለትም  ደህንነት፣ የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ጥቃትን ከማይቀበለው ህዝብ ጋር በመሆን ፍላጐታቸውን ማክሸፍና የህዝቡን የሰላምና ደህንነት ፍላጐት በበቂ መጠን ማርካት ሲቻል የመከላከያን ሃይል በዚህ መጥመድና የህዝቡንም ኑሮ በስጋት የተሞላ ማድረግ አይገባም። ከነዚሁ ሃይሎች ጋር የተሰለፉ ኮንትሮባንዲስቶች በመከላከያው ሃይል ውስጥም ሊኖሩ የሚችሉ መሆኑን መጠርጠር የመንግስት ቁልፍ ተግባር ሊሆን ይገባል። ስለሆነም ሰራዊቱ ከላይ የተመለከቱ ሃገራዊና አህጉራዊ ስራዎቹን ብቻ እንዲሰራ ማድረግ የመጀመሪያው መፍትሄ ነው። በዚህ ተግባር ተሰማርተው የተገኙ ሃይሎች ላይ ወሳኝ እርምጃዎች መውሰድና ይህንንም ለህዝብ ይፋ ማድረግ ሌላኛውና ለተጠናከረው የህዝብ ተሳትፎ መጎልበት ወሳኝ የሚሆነው የመፍትሄ አቅጣጫ ነው።

ከሁሉ በላይ የሆነውና ዋናው መፍትሄ ደግሞ የስርአቱ ቁልፍ ተግዳሮት የሆነውን የኪራይ ሰብሳቢነት አጀንዳ በየጊዜው በመጣበት አግባብ ህዝቡን ዋነኛ ባለቤት በማድረግ፣ በተቀናጀና በተባበረ ስልት ከመሰረቱ ለማስወገድ ሌት ተቀን መስራት እንጂ ለውሃ ቀጠነ የመከላከያ ሰራዊትን ማሰማራት የሰራዊቱን ግዝፈትና እውቅና ከማውረድም በላይ ለኮንትሮባንዲስቱ ሃይል የልብ ልብ መስጠት ስለሚሆን በዚሁ አግባብ እነዚህን እንቅስቃሴዎች ከወዲሁ እንዳይመለሱ አድርጎ መቅጨት ያስፈልጋል። አልያ ግን የሰቆቃው ዘመን የሚራዘም እና ህገ መንግስታዊ ስርአቱም አደጋ ላይ የሚወድቅ ይሆናል።